# ወርሃዊ የአየር ጠባይ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## ከሜይ1-31/2021 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

## እንዲሁም ከጁን 1-30/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ጁን 2021
አዲስ አበባ

ርዕስ　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　ገፅ


እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2021 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ ........ 3

ካርታ 6　እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ 5

ካርታ 7　እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2021 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ........ 6

ካርታ 8　እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ........ 7

እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2021 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻ ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ 8

ካርታ 9　ከሜይ 1 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ 8

እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2021የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ 9

ካርታ 10　እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ 9

........ 9

እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ ........ 10

እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 10

እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 11


# እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2021 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

ባለፈዉ የሜይ ወር ለዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች በተለይም በመጀመሪያዉ አስር ቀናት በመጠናከራቸዉ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተስፋፋ የዝናብ ስርጭት እንዲኖር አስተዋፅኦ አድረጓል። በተጨማሪም ከነበረዉ ጠንካራ የደመና ክምችት በአንዳንድ የደቡብ፣ የደቡብ ምዕራብ እና ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ለወንዞች መሙላት እና ለጎርፍ መከሰት መንስዔ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል። በዚሁ መሰረት በድሬዳዋ አካባቢ የዘነበዉ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ በሰዎች ህይዎት ላይ ጉዳት ማድረሱን የተሰበሰቡ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይሁን እንጂ ወደ ሀገራችን የገባ የነበረዉ ዕርጥበት አዘል አየር ከዕለት ወደ ዕለት በመዳከሙ በተለይም በሶስተኛዉ አስር ቀናት የዝናብ መጠን እና ስርጭት ከአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ቀንሶ ተስተዉሏል፡፡ በአጠቃላይ ባለፈዉ የሜይ ወር በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተለያየ መጠን ያለዉ ዝናብ የተመዘገበ ሲሆን፤ በአንዳንድ ቦታዎች ላይም ለጎርፍ መከሰት መንስኤ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ በተለይም በመጀመሪያዉና በሁለተኛዉ አስር ቀናት ላይ ተመዝግቧል፡፡ ለመጥቀስም በወላይታ ሶዶ 63.2፣ በሳዉላ 31.5፣ 56.7፣ 48.5 እና 40.8፣ በጎዴ 38.0፣ በአርባ ምንጭ 41.3ና 35.7፣ ቡሌ ሆራ 36.1፣ 44.6ና 31.5፣ በነቀምቴ 32.2፣ 67.7፣ 71.7፣ በጊምቢ 43.1 ,31.3, 39.7፣ 41.2፣ በጎንደር 38.9፣ 62.3፣ በባህርዳር 42.2ና 43.9፣ በሶኮሩ 42.7፣ አዋሽ አርባ 90.0፣ በማጀቴ 56.4ና 34.2፣ በአዲስ አበባ 59.8ና 49.3፣ በአቦምሳ 43.7ና 52.2፣ በአርጆ 38.4፣ 31.2፣ 34.4፣ 38.6ና 42.6፣ በአደሌ 42.4፣ በአዴት 54.6፣ በባቲ 39.6፣ በቻግኒ 44.0፣ በጨፋ 37.3፣ በኮምቦልቻ 35.6፣ በድሬዳዋ 82.9ና 46.4፣ በዳንግላ 55.2ና 46.2፣ በገለምሶ 57.2፣ በገዋኔ 40.9፣ በጊኒር 78.0ና 40.0፣ በጎሬ 45.0፣ በሆሳና 32.7፣ በጂግጂጋ 44.9፣ በጅማ 40.2፣ 32.4፣ 32.8፣ በጂንካ 36.4፣ በማሻ 54.2፣ 30.6፣ 31.2፣ 40.2 69.2፣ በማንኩሽ 38.0፣ በሚኤሶ 61.7፣ በመካነሰላም 66.7፣ በአዳማ 39.5፣ በነጆ 46.0ና 35.9፣ በነገሌ 41.1ና 36.1፣ በፓዌ 64.5፣ በወረኢሉ 35.7ና 33.9፣ በያቤሎ 46.3፣ በየትኖራ 37.1፣ 47.0፣ በወራቤ 43.5፣ በአማን 38.7፣ 51.4ና 33.7፣ በጊዳ አያና 32.6፣ 63.8ና 34.8፣ በጎሎልቻ 57.2፣ በዕጊቃ 112.0፣ በድዴሳ 81.0፣ በአይራ 30.2፣ በአየሁ 38.2፣ በቡሬ 50.4፣ በጭራ 36.7፣ በደብረ ታቦር 37.6፣ በደብረወርቅ 32.2፣ በእንዋሪ 40.1፣ በጋቲራ 36.5፣ በሊሙገነት3 31.2, 44.3፣ በሻምቡ 30.1፣ በሻውራ 40፣ በወሊሶ 30.9፣ በጃራ 46.7፣ በቡርጃ 65.4, 42.8፣ በጉንዶ መስቀል 42.3፣ በቡሬ 70.9፣ በፉኝዶ 37.3, 47.5፣ በዳልፋጊ 34.9፣ በተርጫ 34.4 እና በቴፒ 35.2 በሚሜ ይገኙበታል።


ባለፈዉ የሜይ ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ በሲዳማ፣ በሱማሌ ክልል እና ከአፋር ክልል ዞን 3ና 5 ዞኖች ላይ ከ50-410 ሚሜ የሚደርሰ ከ5-23 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ በተቀሩት የሀገሪቱ አካባዎች ላይ ከ5-25 ሚሜ የሚደርስ ከ4 ላነሱ ቀናት ዝናብ ነበራቸዉ፡፡

ባለፈዉ የሜይ ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከትግራይ ክልል ምዕራባዊ ክፍል፣ ከሰሜን ጎንደር ምዕራባዊ ክፍል፣ ከአሶሳና ከማሽ ዞኖች፣ ከቄለም ወለጋ፣ ከጥቂት የባሌና አርሲ እንዲሁም የሲዳማ ክልል ዞኖች ላይ ከተመዘገበዉ ከመደበኛ በታች የሆነ ዝናብ በስተቀር በተቀሩት የሀገሪቱ ክልል ዞኖች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡


ካርታ 6   እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 7    እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2021 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ 8   እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር





ከመደበኛ በታች   መደበኛ   ከመደበኛ በላይ

# እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2021 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻ ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፈዉ የሜይ ወር በአብዛኛዉ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በተለይም በመጀመሪያዉ አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች የእርጥበት ሁኔታው በተለይም በምዕራብ አጋማሽ፣ በምስራቅ አማራ፣ በትግራይ ምስራቃዊ ክፍል፣ በምዕራብ፣ በመካከለኛዉ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች እንዲሁም በሲዳማ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በብዙ ቦታዎች በስርጭትም ሆነ በመጠን ረገድ የተስፋፉ እርጥበት እንደነበራቸዉ ቀሰ በቀስም ወደ ምስራቅና ሰሜን ምስራቅ አካባቢዎች ላይ ጥሩ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸዉ፡፡ ይህም ሁኔታ በተለያዩ የዕድገት ደረጃዎች ላይ ለሚገኙ ልዩ ልዩ የበልግና የረጅም ጊዜ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች የዉሃ ፍላጎት መሟላት እና ለአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽና የመጠጥ ዉሃ አቅርቦት መሻሻል የጎላ ጠቀሜታ ነበረዉ። በተጨማሪም ለረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች የማሳ ዝግጅትና ለዘር እርሻ እንቅስቃሴ ከፍተኛ አስተዋጾ ነበረው፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ ቦታዎች ላይም ለጎርፍ መከሰት መንስኤ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ በተለይም በመጀመሪያዉና ሁለተኛዉ አስር ቀናት ላይ በአማራ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች፣ በምዕራብና ምስራቅ ኦሮሚያ፣ በጋምቤላ እና በቤንሻንጉል ጉሙዝ በአንዳንድ ስፍረዎቻቸዉ ላይ የነበረ ሲሆን፤ በድሬደዋ አካባቢ የጣለዉ ካባድ ዝናብ ቅጽበታዊ ጎርፍና የመሬት መንሸራተት በማስከተል በቋሚ ተክሎች በንብረትና በሰዉ ህይወት ላይ ጉዳት አድርሷል፡፡ ይሁን እንጂ ወደ ሀገራችን እየገባ የነበረዉ ዕርጥበት አዘል አየር ከዕለት ወደ ዕለት በመዳከሙ በተለይም በሶስተኛዉ አስር ቀናት የተስተዋለው የዝናብ ማነስ በተለይም የበልግ ወቅት አብቃይና ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ አካባቢዎች ላይ የእርጥበት እጥረት እንዲፈጠር አድርጓል (ካርታ 9)፡፡


ካርታ 9 ከሜይ 1 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2021የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ ከሜይ 1-31-2021 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በአብዛኛው አባይ፣ ባሮ አኮቦ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ስምጥ ሸለቆ እና የላይኛው ዋቢ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ ከእርጥበታማ እስከ ከፍተኛ እርጥበት ሁኔታ የተስተዋለባቸው ናቸው። በሌላ በኩል በመካከለኛው ተከዜ፣ አባይ፣ የታችኛው ገናሌዳዋ፣ የታችኛውና የላይኛዉ አዋሽ እና የታችኛው ባሮ አኮቦ ተፋሰሶች ደግሞ መጠነኛ እርጥበት ሁኔታ እንደነበራቸው ተስተውሏል። የተቀሩት ተፋሰሶች ደረቅና ከፊል ደረቅ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው እንደነበር ተስተውሏል (ካርታ 10) ።

ካርታ 10 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

በመደበኛው ሁኔታ ወቅታዊው የክረምት ዝናብ ቀደም ብሎ በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚጀምር ሲሆን፤ በሂደትም እየተጠናከሩ ከሚሄዱ የክረምት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ጋር ተያይዞ በጁን ወር ውስጥ የተቀሩትን የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን ያዳርሳል፡፡

በመጪው የጁን ወር ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለይም በደቡብ ምዕራብ የሃገሪቱ ቦታዎች ላይ ዝናቡ በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተሻለ ሊሆን እንደሚችልና ከጁን አጋማሽ በዋላ ዝናቡ ቀስ በቀስ ወደ ምዕራብና ሰሜን ምዕራብ አከባቢዎች ላይ ሊስፋፉ እንደሚች የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

<u>በአጠቃላይ በሚቀጥለው የጁን ወር ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ እና ምእራብ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ የደቡብና የምዕራብ የሸዋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ምዕራብና ምሥራቅ ጎጃም፣ አዊ ዞን፣ የሰሜንና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ የባህር ዳር ዙሪያ፤ ከትግራይ ክልል የምዕራብና የሰሜን ምዕራብ ዞኖች፤ የጋምቤላና የቤንሻንጉል ዞኖች በተጨማሪም የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል አብዛኛው ዞኖች ከመደበኛው ጋር የተቀራረበና አልፎ አልፎም በአንዳንድ ቦታዎቻቸው ላይም ከመደበኛ በላይ ዝናብ ያገኛሉ። በተጨማሪም ሊጠናከሩ እንደሚችሉ ከሚጠበቁ የደመና ክምችቶች በጥቂት የምዕራብ የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራል። በአንጻሩ ከኦሮሚያ የጉጂ፣ አርሲና ባሌ፣ ምዕራብ እና ምሥራቅ ሐረርጌ ዞኖች በአንዳንድ ቦታዎቻቸው ላይ አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ እንደሚያገኙ የሚጠበቅ ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች ግን ደረቅ ሆነው ይሰነብታሉ።</u>

## እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ የጁን ወር የበልግም ሆነ የመኸር እርሻ እንቅስቃሴ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሚከናዎንበት ወቅት ሲሆን፤ በተለይም የክረምት ዝናብ ከምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ አካባቢዎች ጀምሮ ወደ ሰሜን ምዕራብና ወደ ሰሜን የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚስፋፋበት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የማሳ ዝግጅትና የዘር መዝራት ተግባራት በስፋት የሚስተዋልበት ጊዜ ነው፡፡

በመጪው የጁን ወር ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ጥሩ የሆነ የእርጥበት ይዘት እንደሚኖራቸውና በተለይም በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ ዝናቡ በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተሻለ ሊሆን እንደሚችልና ከጁን አጋማሽ በኋላም ቀስ በቀስ ወደ ምዕራብና ሰሜንምዕራብ አከባቢዎች ላይ ሊስፋፉ እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

ይህም ሁኔታ ለግብርና ስራ እንቅስቃሴ የተለያየ ጠቀሜታ እንደሚኖረው የሚታመን ሲሆን፤ ከዚህም ጋር ተያይዞ የመኸር ሰብል አብቃይ በሆኑ አካባቢዎች የአፈር ውስጥ እርጥበትን የሚያሻሽል ከመሆኑ አንፃር የማሳ ዝግጅት ለማከናወንም ሆነ የመኸር ሰብሎችን በወቅቱ ለመዝራት ምቹ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡ እንዲሁም አስቀድመው ተዘርተው በተለያዩ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙና እድገታቸውን ላልጨረሱ የበልግ ሰብሎችም ሆነ በኤፕሪል እና በሜይ ወር ለተዘሩ የረጅም ጊዜ ሰብሎች የሚገኘው እርጥበት በጎ ሚና ይኖረዋል፡፡ በሌላ በኩል በመጠን ዝቅተኛ ቢሆንም፤ በተለያዩ የሰሜን ምስራቅና የምስራቅ የአርብቶ አደር አካባቢዎች በወሩ ከሚጠበቀው እርጥበት ተጠቃሚ እንደሚሆኑና የመጠጥ ውሃና የግጦሽ ሳር አቅርቦታቸው እንደሚሻሻል ይጠበቃል፡፡ በአንፃሩ በተወሰኑ የምዕራብ የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ ከሚጠበቀው ከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ የጎርፍ መፈጠር ሊኖር ስለሚችል ይህም ሁኔታ የአፈር መሸርሸርና የመሬት መንሸራተትን እንዳያስከትል አስፈላጊው ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተለይም በተከታታይ ዝናብ እያገኙ ያሉ አካባቢዎች ልዩ ትኩረት እንዲያገኙ ይመከራል፡፡

## እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው የጁን ወር ብዙዎቹ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ ተፋሰሶች ላይ እንደሚያዳርስ ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም አብዛኛዎች ተፋሰሶች የወቅቱን ዝናብ እንደሚያገኙና በተለይም ቀደም ብለው ማግኘት በጀመሩት የምዕራብ አጋማሽ ተፋሰሶች ላይ በስርጭትም ሆነ በመጠን የተሻለ እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚህ ጋር ተያይዞ በአብዛኛው አባይ፣ ኦሞጊቤ፣ ባሮአኮቦ፣ የመካከለኛው ስምጥሸለ፣ ተከዜ፣ የላይኛው ገናሌዳዋ ፣ ዋቢሸበሌ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ የሚጠበቁ ሲሆን፤ በሌላ በኩል የመካከለኛውና የታችኛዉ ገናሌዳዋ፣ የላይኛው ዋቢሸበሌ ምስራቃዊ አዋሳኝ ተፋሰሶች በጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ መጠነኛ እርጥበት ይጠበቃል። ከዚህ ጋር ተያየዞ የክረምቱ ዝናብ በመጀመሩ ለጎርፍ ተጋላጭ የሆኑ ተፋሰሶች ትኩረትና ክትትል መስጠት አስፈላጊ ይሆናል፡፡